GSMA

# የስልክ በይነመረብ ክህሎቶች የሥልጠና መርጃ ስብስብ

ሰዎችን መደበኛ የስልክ በይነመረብ ክህሎቶችን ለማስተማር የተዘጋጀ መመሪያ



የቅጂ መብት © 2024 GSM Association

# ሞጁል 4፦ Google

## የስልክ በይነመረብ ክህሎቶች የሥልጠና መርጃ ስብስብ


ሰዎችን መደበኛ የስልክ በይነመረብ ክህሎቶችን ለማስተማር የተዘጋጀ መመሪያ

## ይህ ምንድን ነው?

**በስልኩ ላይ Google ፍለጋን ያሳዩ።**

**ያብራሩ፡-** «Google ፍለጋ መረጃ ለማግኘት ያግዝዎታል። ለማግኘት የሚፈልጉትን መረጃ ለምሳሌ፣ «ንግድን እንዴት መጀመር እንደሚቻል» ወይም «አንድን ምግብ እንዴት ማዘጋጀት እንደሚቻል» ለGoogle ይንገሩት እና እርስዎ የሚፈልጉትን ለማግኘት ሰዎች በይነመረብ ላይ ያስቀመጧቸውን መረጃዎች በሙሉ ይፈልጋል።»

## የሚያስፈልጉዎ ቁሳቁሶች፡-



ስማርት ስልክ ቀፎዎች




የGoogle ፖስተር

## ለምን ሊጠቀሙበት ይችላሉ?

«ሥራን፣ የምግብ አሰራሮችን፣ ፊልሞችን፣ ዘፈኖችን፣ ዜናን የሚመለከት መረጃ ወይም ስለ ትምህርት ቤት ወይም ኮሌጅ መረጃ ሊያገኙበት ይችላሉ።»

«መረጃውን ለማግኘት የትም መሄድ አይጠበቅብዎትም፣ ሁሉም በስልክዎ ላይ ባለ በይነመረብ አማካኝነት ይገኛል።»

ስለ Google ጥቅሞች እና በግልዎ እንዴት እንደሚጠቀሙበት የራስዎን ምሳሌዎች ለሰልጣኙ ያጋሩ።

## ለምን ሊጠቀሙበት ይችላሉ?

**ለሰልጣኙ ሕይወት እንዴት** ጠቃሚ ሊሆን እንደሚችል በመወያየት ከሰልጣኙ ጋር የሚገናኝ እንዲሆን ያድርጉት። ለሚከተሉት የሰልጣኝ ዓይነቶች ተገቢ የሆኑ ምሳሌዎችን ታሳቢ ያድርጉ፦

**አዛውንት፦** ስለ ዜናዎች፣ ስብከቶች፣ የመዝናኛ ፕሮግራሞች እና ሙዚቃ፤ የምግብ አሰራር መመሪያዎችን ለማግኘት፤ አካባቢያዊ ዜናዎችን ለማንበብ ቪድዮዎችን ይፈልጉ እና ይመልከቱ።

**እናት ወይም የቤት እመቤት፦** አዲስ የምግብ አሰራር ለመማር፤ ቤትዎን ወይም ንግድዎን ለማስተዳደር፤ ልጆችዎን በጤናቸው እና በትምህርት ሥራቸው ለማገዝ፤ ልብሶችን ለማስተካከል እና ለሌሎችም ጽሑፎችን እና ቪድዮዎችን ይፈልጉ።

**የንግድ ባለቤት፦** ንግድዎ እንዴት ማስመዝገብ እና ማስተዳደር እንደሚቻል እና የመሳሰሉ አዳዲስ ነገሮችን ይማሩ፣ ይወቁ፤ አዲስ የምግብ አሰራር መመሪያዎችን፣ የፀጉር አሰራሮችን፣ የአለባበስ አይነቶችን፣ የጥገና ዘዴዎች ወዘተ የመሳሰሉ ጠቃሚ ምክሮችን እና ሃሳቦችን ከሌሎች የንግድ ባለቤቶች ያግኙ።

**ገበሬ ወይም የገጠር ሰው፦** ሰብሎችን ለማብቀል፣ ከተባዮች ለመከላከል፣ በተለያዩ ወቅቶች ሰብሎችን ለመለወጥ እና አፈር ጤናማ ሆኖ እንዲቆይ ለማድረግ የተሻሉ ዘዴዎችን ለመማር ቪዲዮዎችን ይመልከቱ። ይህ ተጨማሪ ምግብ እንዲያመርቱ እና ለወደፊቱ መሬቱን በጥሩ ሁኔታ እንዲንከባከቡ ያግዝዎታል።

**ወጣት፦** በትምህርትዎ እገዛ ለማግኘት ወይም ሥራ ለማግኘት ወይም ንግድ ለመጀመር አዳዲስ ክህሎቶችን ለመማር ቪዲዮዎችን ይመልከቱ፤ በሲቪዎ ላይ እገዛ ለማግኘት ወይም ሥራ ለማግኘት ጽሁፎችን ያግኙ፤ የሚወዱት ተዋናይ ወይም ዘፋኝን ቪድዮዎች ይመልከቱ፤ በአካባቢዎ ስላለ ስፖርት ወይም ስለሚወዱት የስፖርት ቡድን ወቅታዊ መረጃ ይፈልጉ።

## እንዴት ነው የሚሰራው?

### ስልኩን በሰልጣኙ እጅ ላይ ያድርጉት እና ቅደም ተከተሎችን እንዲከተሉ ያግዟቸው።




**ፖስተሩን ያሳዩ** እና ለቀላል ፍለጋ ለምሳሌ፣ የአካባቢውን ታዋቂ ስፍራ ወይም ዝነኛ ሰው ለመፈለግ ቀላል ቅደም ተከተሎችን ይከተሉ።

**ያብራሩ፦** «የድምጽ ፍለጋዎችን ለማድረግ ማይክራፎን መጠቀም ይቻላል:::: ምንም ጽሑፍ መጻፍ አይጠበቅብዎትም።»

**ማይክራፎኑን በተግባር ያሳዩ፦** የት እንደሚገኝ እና እንዴት ጥቅም ላይ ማዋል እንደሚቻል።

## ልምምድ ያድርጉ!

**«አሁን ስለ Google ፍለጋ አውቀዋል፣**
**ምን ለማድረግ ሊጠቀሙበት ይፈልጋሉ?»**

ሰልጣኙ በፍላጎታቸው መሠረት የሚፈልጓቸውን ቁልፍ ቃላት ይስጧቸው። አንድ ወይም ሁለት ቃላትን በመጠቀም ፍለጋውን ቀላል ለማድረግ ይሞክሩ።

ሰዎች ፍለጋ እንዲያደርጉ የሚያስችሉ Googleን የሚመስሉ ሌሎች አገልግሎቶች እንዳሉ **ያብራሩ**። ለዚህ አንዳንድ ምሳሌዎች Yahoo እና Bing ናቸው።

## ደህንነት

«በበይነመረብ ላይ በርካታ ጥሩ መረጃዎች አሉ፣ ነገር ግን አንዳንዶቹ ደግሞ ያን ያህል ጥሩ አይደሉም፤ አንዳንዶቹ ደግሞ እውነተኛ ያልሆኑ ናቸው። ሁልጊዜም ለሚፈልጉት ነገር የተሻለውን መልስ ለማግኘት ቢያንስ ከሁለት እስከ ሦስት ውጤቶችን ወይም ድረ ገጾችን መመልከት የተሻለ ነው።»

«በአንዳንድ ድረ ገጾች ላይ የምዝገባ ቅጽ በመሙላት ወይም መለያ በመፍጠር እና በመሳሰሉ መንገዶች መረጃዎችን እንዲያጋሩ ሊጠየቁ ይችላሉ። እንደ የተንቀሳቃሽ ስልክ ባንክ ቁልፍ ወይም የሚኖሩበት ቦታ የመሳሰሉ የግል መረጃዎችን በመስመር ላይ በጭራሽ አያጋሩ።»



**«በመስመር ላይ ደህንነትዎን ለመጠበቅ ምርጥ ጠቃሚ ምክሮች» የሚለውን ፖስተር ያሳዩ።**

እነዚህ ጠቃሚ ምክሮች Googleን ሲጠቀሙ ምን ማለት እንደሆኑ ከሰልጣኞችዎ ጋር **ይወያዩ**። ለሰልጣኝዎ ተገቢ የሆኑ ምሳሌዎችን በመጠቀም ጠቃሚ ምክሮቹ ህይወት እንዲኖራቸው ያድርጉ። ምሳሌ፣ የተወሰኑ ሰዎች Google ላይ ስለሚገኙ አንዳንድ ይዘቶች ሊጨነቁ ይችላሉ። አንዳንድ ሰዎች Google ስለሚጠቀሙ አጭበርባሪዎች ሊጨነቁ ይችላሉ፤ አንዳንድ ሴቶች ደግሞ ትንኮሳን እንዴት መከላከል እንደሚችሉ የበለጠ ሊያሳስባቸው ይችላል።

አጭር ሥልጠና፦
Google

# ፖስተሮች እና ተቆርጠው የወጡ ማሳያዎች

## የስልክ በይነመረብ ክህሎቶች የሥልጠና መርጃ ስብስብ

ሰዎችን መደበኛ የስልክ በይነመረብ ክህሎቶችን ለማስተማር የተዘጋጀ መመሪያ

GSMA

# በመስመር ላይ ደህንነትዎን ለመጠበቅ ምርጥ ጠቃሚ ምክሮች

**በይነመረብ በዓለም ዙሪያ ላሉ ሰዎች ሁሉ ክፍት መሆኑን ያስታውሱ፣ ስለዚህ እንደ እውነተኛው የህዝብ መገናኛ ቦታ (ለምሳሌ፣ የገበያ ቦታ) ማየቱ አስፈላጊ ነው እንዲሁም ራስዎን በመጠበቅ እና በመስመር ላይ ለሚያደርጉት ነገር ኃላፊነት በመውሰድ ደህንነትዎን ይጠብቁ።**

## በመስመር ላይ የሚመለከቱት ነገር ሁሉ እውነት እንዳልሆነ ያስታውሱ

ማንኛውም ሰው ማንኛውንም ነገር በመስመር ላይ መለጠፍ ይችላል፣ ስለዚህ የሚመለከቱትን ሁሉ አይመኑ። ከሚያምኑት ሰው እንኳን ቢሆን እውነት ላይሆን ይችላል። መረጃን ለሌሎች ከማጋራትዎ በፊት ጥንቃቄ ያድርጉ።

## በመስመር ላይ ለተዋወቁት ሰው ገንዘብ ከመላክዎ በፊት ደግመው ያስቡ

ያልጠየቋቸውን ኢሜይሎች፣ መልዕክቶች ወይም ብቅ-ባዮች በተለይም ገንዘብ የሚጠይቁ ከሆኑ ወይም እንግዳ የሆኑ አገናኞችን ከያዙ ይጠንቀቋቸው።

## የይለፍ ቃሎችን ጨምሮ የግል መረጃዎን ለግልዎ ያቆዩ

በጣም አስፈላጊ ካልሆነ በቀር፣ እንደ ሙሉ ስምዎ፣ የቤት አድራሻዎ ወይም ስልክ ቁጥርዎ ያሉ የግል ዝርዝሮች ማጋራት የለብዎትም።

## በመስመር ላይ በሚገኙ ሌሎች ሰዎች ላይ ጉዳት አያድርሱ

መልካምነትን እና አክብሮትን ያሳዩ። ጉልበተኝነት አያሳዩ፣ የውሸት መረጃን አያሰራጩ ወይም ማንም ሰው ላይ ትንኮሳ አያድርሱ። በመስመር ላይ የሚወስዷቸው እርምጃዎች በእውነተኛ ሕይወት ላይ ያሉ ሰዎች ላይ ተጽዕኖ ሊያሳድሩ ይችላሉ።


## ማጭበርበሮችን እና አጭበርባሪዎችን ይወቁ

ልክ በእውነተኛ ሕይወት እንዳለው ሁሉ፣ በበይነመረብ ላይም ሌቦች እና ወንጀለኞች አሉ። አንዳንድ ሰዎች በመስመር ላይ ሌላ ሰው እንደሆኑ ያስመስላሉ።


## የሚያስቸግርዎትን ሰው በማገድ ወይም ችላ በማለት እርምጃ ይውሰዱ

የሆነ ሰው በመስመር ላይ ካስቸገረዎ ወይም ትንኮሳ ካደረሰብዎ፣ እርዳታ ይጠይቁ እንዲሁም ለሆነ ሰው ይናገሩ ወይም ሪፖርት ያድርጉ።

# የዳታ ወጪዎች




# Google እንዴት መጠቀም እንደሚቻል



ተቆርጠው የወጡ ምልክቶች
Google


ተቆርጠው የወጡ ምልክቶች
Google




ተቆርጠው የወጡ ምልክቶች
Google



ተቆርጠው የወጡ ምልክቶች
Google



ተቆርጠው የወጡ ምልክቶች
Google



ተቆርጠው የወጡ ምልክቶች
Google